## የኢኮኖሚ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ተግባር እና ኃላፊነቶች

የኢኮኖሚ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ተጠሪነቱ ለወንጀል ጉዳዮች ዘርፍ ሆኖ በስሩ የኢኮኖሚ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክትረ እና ዐቃቢያነ ሕግ እንዲሁም አስተዳደር ሰራተኞችን የያዘ ነው፡፡

ዳይሬክቶሬቱ በወንጀል ጉዳዮች ዘርፍ ስር ካሉት ዳይሬክቶሬቶች ጋር በወል የተሰጡ ተግባር እና ኃላፊነቶች አሉበት፡፡ ይኸውም፤ የወንጀል ጉዳዮችን በተመለከተ፡-

- በፌድራልም ሆነ በክልል ፖሊስ በተጣራ የምርመራ መዝገብ ላይ መርምሮ መወሰን፣ ተከራክሮ ማስወሰን፤ በፖሊስ የተጀመረ የኢኮኖሚ ወንጀል ምርመራ የምርመራ አካሄዱን ሕጋዊነት ይከታተላል፣ ይመራል፣ በተጀመረ የወንጀል ምርመራ ላይ ሪፖርት እንዲቀርብና ምርመራው በአግባቡ ተከናውኖ እንዲጠናቀቅ ያደርጋል፤
- በሕዝብ ጥቅም መነሻነት ወይም በወንጀል የማያስጠይቅ ሁኔታ መኖሩ በግልፅ ሲታወቅ የወንጀል ምርመራ እንዲቋረጥ ወይም የተቋረጠ የወንጀል ምርመራ እንዲቀጥል ሊያደርግ ይችላል፣ ምርመራው በሕግ መሠረት መከናወኑን ያረጋግጣል፣ ከነዚሁ ተግባራት ጋር በተያያዘም ለፖሊስ ወይም ወንጀል ለመመርመር ሥልጣን ለተሰጠው ሌላ አካል አስፈላጊውን ትእዛዝ ይሰጣል፤
- በምርመራ መዛግብት ጥናትና ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ ከፖሊስ በኩል ተፈላጊውን ድጋፍ ሊጠይቅ ይችላል፣ በወንጀል መዛግብት ላይ የተሰጡ የዓቃቤ-ሕግና የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን ለሚመለከተው ፖሊስ ያሳውቃል፣ የወንጀል ምርመራ መዛግብትን አስመልክቶ በየደረጃው ዓቃብያነ-ሕግ በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ በፖሊስ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ተቀብሎ ያጣራል፣ ውሳኔዎችን ይሰጣል፤
- በስር ዓቃብያነ-ሕግ የተሰጡ የክስ አያስቀርብም ውሳኔዎችን ይመረምራል፣ ግድፈት ያጋጠመው እንደሆነም ወዲያውኑ እንዲታረም ያደርጋል፣ የተጠናቀቁ የምርመራ መዛግብትን ከሕግና ከማስረጃ አንፃር መርምሮ የአያስከስስም ውሳኔ ይሰጣል፤
- የእጅ ተፈንጅ ወንጀሎች ተፈጽመው ሲገኙ በተፋጠነ ሥነ-ሥርዓት ውሳኔ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ለዚህም ከፖሊስና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ጋር ተባብሮ ይሠራል፤
- ለወንጀል ጉዳይ ምስክሮች በወቅቱ መጥሪያ እንዲያደርስና ምስክሮችንም ወደ ፍርድ ቤት እንዲያቀርብ ለፖሊስ ትእዛዝ ይሰጣል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም የዓቃቤ-ሕግ ምስክሮች ተገቢውን ጥበቃ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

- ፍርድ ቤቶች በወንጀል ጉዳይ የሚሰጧቸው ውሳኔዎችና ትዕዛዞች መፈጸማቸውንና መከበራቸውን ይከታተላል፣ ሳይፈጸሙ ከቀሩ ወይም አፈጻጸማቸው ሕግን ያልተከተለ ከሆነም በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ለሰጠው ፍርድ ቤት በማመልከት የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

ከላይ በጥቅል የተቀመጡቱ ተግባርና ኃላፊነቶችን መሰረት በማድረግ ዳይሬክቶሪቱ በዋናነት ኢኮኖሚያዊ ይዘት ያላቸዉ ሆነዉ በሀገር፣ በመንግስት፣ እንዲሁም በግለሰቦች ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ወንጀሎችን ይመለከታል፡፡ በመሆኑም በወንጀል ህጋችን እና በተለያዩ አዋጆች ዉስጥ የተጠቀሱ በግለሰብ፣ በመንግስት እና በሀገር ንብረት እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች ላይ የሚፈፀሙ እና ጉዳት የሚያደርሱ ዋና ዋና ወንጀሎችን የማየት ተግባር እና ኃላፊነት ያለበት ሲሆን በዳይሬክቶሬቱ የሚታዩ ዝርዝር ወንጀሎች ከዚህ በታች ተመላክተዋል፡፡

- ከንግድ ዉድድር እና የሸማቾች መብት ጋር የተገናኙ ወንጀሎች፤
- ከፍትህ ሚንስትር በውክልና ከተሰጡ የገቢዎችና ጉምሩክ ወንጀሎች፤
- ከንግድ ምዝገባና ፍቃድ ጋር በተያያዘ የሚፈፅሙ ወንጀሎች፤
- የታወቁ ማህተሞችን፣ ቴምብሮችን፣ ምልክቶች፣ ሚዛኖችንና መለኪያዎችን ወደ ሀሰት መለወጥ ወንጀሎች፤
- የኮንትሮባንድ ወንጀሎች፤
- የአራጣ ወንጀል፤
- እሽግ መፍታት እና ምልክቶችን ማንሳት ወንጀሎች፤
- የጉምሩክ ቁጥጥርን ማሰናከል ወንጀል፤
- ከንግድ ምልክት እና ሌሎች የአዕምሯዊ ንብረት ጥበቃ ጋር በተያያዙ የሚፈፀሙ ወንጀሎች፤
- የታወቁ ገንዘቦች፣ የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች፤
- የደረቅ ቸክ ወንጀል፤
- የከበሩ ማዕድናት ዝውውር ወንጀሎች፤
- ሀሰተኛ ገንዘብ ህትመትና የውጪ ሀገር ገንዘብ ዝውውር ወንጀል፤ እና መሰል ኢኮኖሚያዊ ጉዳት የሚያደርሱ ወንጀሎችን ያያል፡፡